ንብ ኢንተርናሽናል ባንክ
Nib InternationalBank

የስብሰባ ጥሪ

የንብ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ.
የባለአክሲዮኖች 27ኛ መደበኛ እና 22ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ጥሪ

ንብ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ. ቅዳሜ ህዳር 19 ቀን 2019 ዓ.ም አዲስ አበባ ካዛንቺስ አካባቢ በሚገኘው ኢንተር ሌግዠሪ ሆቴል ከጠዋቱ 2:00 ሰዓት ጀምሮ በኢፌዲሪ ንግድ ሕግ አንቀጽ 366(1)፣ 367(1) እና 370 እንዲሁም በባንኩ የተሻሻለ መመስረቻ ጽሁፍ አንቀፅ 14(2እና 4) መሰረት የንብ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ. ባለአክሲዮኖች 27ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ እና 22ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ቅዳሜ ህዳር 19 ቀን 2019 ዓ.ም ከጠዋቱ 2፡00 ሰዓት ጀምሮ፣ አዲስ አበባ ካዛንቺስ አካባቢ በሚገኘው ኢንተር ሌግዠሪ ሆቴል ስለሚካሄድ፣ ባለአክሲዮኖች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተጠቀሰው ቀን፣ ሰዓት እና ቦታ በስብሰባው ላይ እንዲገኙ የዳይሬክተሮች ቦርድ አክብሮታዊ ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡

1. የአክሲዮን ማኅበሩን የሚመለከቱ ዋና ዋና መረጃዎች

1.1. የአክሲዮን ማህበሩ ስም፡- ንብ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ.

1.2. የአክሲዮን ማኅበሩ ዋና መሥሪያ ቤት አድራሻ፡- አዲስ አበባ፣ ልደታ ክ/ከተማ፣ ወረዳ 09፣ የቤት ቁጥር አዲስ

1.3. የአክሲዮን ማኅበሩ ድረ-ገፅ፡- https://www.nibbanksc.com

1.4. የአክሲዮን ማኅበሩ የምዝገባ ቁጥር፡- kk/AA/2/0000814/2004

1.5. የአክሲዮን ማኅበሩ የተፈረመ ዋና ገንዘብ (ካፒታል)፡- ብር 7,847,553,500.00

1.6. የአክሲዮን ማኅበሩ የተከፈለ ዋና ገንዘብ (ካፒታል)፡- ብር 7,847,553,500.00

2. ለባለአክሲዮኖች 27ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ የቀረቡ አጀንዳዎች

2.1. የዳይሬክተሮች ቦርድ የጥቆማ እና አስመራጭ ጊዜያዊ ኮሚቴ አባላትን መምረጥ፣

2.2. እስከ ጥቅምት 30 ቀን 2019 ዓ.ም ድረስ የተደረጉ የአክሲዮን ዝውውሮችን መቀበል፤

2.3. የዳይሬክተሮች ቦርድን እ.ኤ.አ. የ2025/26 የሂሳብ ዓመት ዓመታዊ ሪፖርት ማዳመጥ፣

2.4. የባንኩ የውጭ ኦዲተርን እ.ኤ.አ. የ2025/26 የሂሳብ ዓመት ሪፖርት ማዳመጥ፣

2.5. ከላይ በተራ ቁጥር 2.3 ላይ በቀረበው የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት ላይ ተወያይቶ ማፅደቅ፣

2.6. ከላይ በተራ ቁጥር 2.4 ላይ በቀረበው የውጭ ኦዲተር ሪፖርት ላይ ተወያይቶ ማፅደቅ፣

2.7. እ.ኤ.አ. የ2025/26 የሂሳብ ዓመት የተጣራ ትርፍ አደላደልና አከፋፈል ላይ ተወያይቶ መወሰን፣

2.8. እ.ኤ.አ. የ2025/26 የዳይሬክተሮች ቦርድን ዓመታዊ የአገልግሎት ክፍያ እና እ.ኤ.አ. የ2026/27 ወርኃዊ የአበል ክፍያ መወሰን፤

2.9. የባንኩን የውጭ ኦዲተሮች ሹመት ማፅደቅ እና የአገልግሎት ክፍያ መወሰን፣

2.10. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምርጫን ማካሄድ፣

2.11. ከባንኩ የቀድሞ ዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ክስ ጋር በተያያዘ በቦርዱ በሚቀርበው የውሳኔ ሐሳብ ላይ ተወያይቶ መወሰን፣

3. ለባለአክሲዮኖች 22ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ የቀረበ አጀንዳ

3.1. የባንኩን መመስረቻ ጽሁፍ ለማሻሻል በሚቀርበው የውሳኔ ሐሳብ ላይ ተወያይቶ መወሰን፣ (የተሻሻለው መመስረቻ ጽሁፉ ረቂቅ ከባንኩ ድረ-ገፅ ማግኘት ይቻላል)

4. ማሳሰቢያ

4.1 በጉባኤው ላይ መገኘት የማትችሉ ባለአክሲዮኖች ለተወካዮቻችሁ ሥልጣን ባለው የመንግሥት አካል ተረጋግጦ የተሰጠ የውክልና ሰነድ ዋናውን እና ፎቶ ኮፒ በመያዝ ወይም ውክልና ለመስጠት ሥልጣን ወዳለው አካል ዘንድ መሄድ ሳይጠበቅባችሁ፣ በንግድ ሕጉ አንቀፅ 377 መሰረት ከህዳር 07 ቀን 2019 ዓ.ም እስከ ህዳር 18 ቀን 2019 ዓ.ም ድረስ አዲስ አበባ ሜክሲኮ ራስ አበበ አረጋይ ጎዳና በሚገኘው የንብ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ. ዋና መሥሪያ ቤት 3ኛ ፎቅ የባንኩ የባለአክሲዮኖች አስተዳደር ዋና ክፍል በአካል በመቅረብ ለዚሁ ዓላማ በባንኩ የተዘጋጀውን የውክልና ቅፅ ሞልተው በመፈረም ተወካይ መሾም እና ተወካዩም ዋናውን የውክልና ማስረጃ በመያዝ በጉባኤው ተካፋይ ለመሆንና ድምፅ ለመስጠት የሚችል መሆኑን እንገልፃለን፡፡ ሆኖም አንድ ባለአክሲዮን ለባንኩ ጠቅላላ ጉባኤ በማንኛውም ችሎታ መወከል የሚችለው አንድ ሰው ብቻ መሆኑን በማክበር እንገልፃለን፡፡

4.2. ባለአክሲዮኖች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በጉባኤው ላይ ለመሳተፍ ሲመጡ፣ ማንነታቸውን የሚያረጋግጥ የታደሰ የነዋሪነት መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም መንጃ ፈቃድ ወይም የፋይዳ መታወቂያ ዋናውን ከፎቶ ኮፒ ጋር በመያዝ በጉባኤው ላይ መሳተፍ የሚችሉ ሲሆን፣ ተወካዮች የውክልናውን ሰነድ ዋናውን ከአንድ ፎቶ ኮፒ ጋር ይዘው መቅረብ እንዳለባቸው በማክበር እንገልፃለን፡፡

4.3. በማንኛውም የባለአክሲዮኖች ጉባኤ ላይ አንድ ሰው የራሱን ጨምሮ በውክልና ድምፅ ሲሰጥ፣ የሚወክለው የአክሲዮን መጠን፣ ከባንኩ ጠቅላላ የተፈረመ ካፒታል ውስጥ ቢበዛ ከአሥር በመቶ (10%) መብለጥ የለበትም፡፡

4.4. የባንኩ የቦርድ አባላት እና የባንኩ ሰራተኞች በየትኛውም የባለአክሲዮኖች ጉባኤ ላይ ማንኛውንም ባለአክሲዮን ወክለው መሳተፍ የማይችሉ መሆኑን በማክበር እንገልፃለን፡፡

የዳይሬክተሮች ቦርድ
ንብ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ.

ይሠራል ከልብ፣
እንደ ንብ!
Committed to Service Excellence!